# <u>ተአምረ - አሸንዳ</u>

ሰለሞን ሽፈራው

ልክ እንዲህ እንደሰሞኑ፣ በዕንቁጣጣሽ ዋዜማ

የኢትዮጵያዊ ሴትነት፣ ህብረ ዝማሬ ሲሰሚ..

በቅድስት ምድር ህዝቦች፣ የማንነት ዕልፍኝ ጓዳ

ለነጠረ ድንቅ ባህል፣ ዘብ የቆሙቾ |ጓል ኣሸንዳ´

እንደቅም ሴት  አያቶቿ፣ እንደነ ንግሥት ማክዳ

በሐፃን ዘር ረቂቅ ጥበብ፣ ተከሽኖ እሚኳናዳ

የኢትዮጵያ ልጅ ቁንጅና፣ ወብት ከምንጩ ሲቀዳ

ድንገት ትዕይንቱ ማስጧት ፣ በአካል ከሰሜይ ወርዳ

ወደቅድስት እናት ሀገር፣ የመጣቾ < ጥቁር > ዕንግዳ . . .

ከወጣት ዕንስቶች ጋራ

ተመሳስላ– ህብር ፈጥራ

ከነሱ ዕኩል ተሽቀርቅራ

እንደነ ንግስተ –ሳባ

ፀጉሯን |ጎዲን ጤል´ ሹሩባ

ተሰርታውአምራ ተወባ

ጥዑም ዜማ እያወረደች ፣ በቆነጃጅት ተከባ

ለቅድስቲቱ እናት ሀገር ፣ አዲስ ዘመን ልታጠብ . . .

|ኣደዋዬ ኣደዋኒ

ኩሕል –ጥስም አብልኒ

ምሣዘተይ ኺይበልፃኒ

ብኣል ፈረስ ኺይሃልፈኒ . . . !´

እያለች እርጥብ ቄጠማ

(ያዲስ ዘመን ብሩህ ተስፋ)

ወገቧ ላይ አገልድማ
ከወጣት ቆነጃጅት ጋር፣ በዕንቁጣጣሽ ዋዜማ
በእያንዳንዱ ሰው ቤት ደጃፍ፣ ለፍፁም ደስታ ታድማ
ወላዲት አምላክ ራሷ፣ ልክ እንዲህ እንደ ሰሙ
ልጃገረድ ተመስላ፣ ስትከሰት በዕውኑ. . .
ከወይዛዝርቱ መካከል፣ ጥልፍ ቀሚሷን አጥልቃ
ለቀየው ላድባሩ ታምና፣ ያንገት ማዙቧን አጥብቃ
እንደብርቋ የመስቀል ወፍ፣ አንድ ዓመት ሙሉ ተናፍቃ
ለተአምር ስትከሰት፣ ስትመጣ ቃሏን ጠብቃ. . .
ስልጣኔ ካልበረዘው፣ ዕፁብ ድንቅ ያገር ባህል
ከኢትዮጵያዊ ማንነት፣ በሚጨልፍ ጠይም ፀዳል
የተስፋይቱን ምድር ህዝቦች፣ ወብት ድምቀት ተሸልማ
ባገሬ ልጆች ሴትነት፣ የደም ገንቦ ተሸክማ
ከዕልፍ አዕላፍ ቆነጃጅት ጋር፣ እርጥብ ቄጠማ አሸርጣ
በያንዳንዳችን ቤት ደጃፍ፣ ስትወርድ ስትወጣ
|. . . ኣዋልደዬ ሎሚ ዕበዳ፣
ላዕላይ ሰማይዶ ኣለወ ማይዳ !?´
እያለች ቅኔ ስትዘርፍ፣ እንደሀበሻ ኮረዳ . . .
ድንግል ማርያም ላንድ ሰሞን፣ በአካል ከሰማይ ወርዳ
ሰፈሩን ስትቦርቅበት፣ ሞት ነው ለካስ አሸንዳ!!

ነሐሴ 19 ቀን 2002 ዓ/ም
አላማጣ